# የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል

# Catering And Tourism Training Center

*ዜና መጽሔት*

ቅጽ 2 ቁጥር 6





## ማዕከሉ ለ52ኛ ጊዜ 128 ሰልጣኞችን አስመረቀ

የማሠልጠኛ ማዕከሉ ዘንድሮ ለሁለተኛ ዙር በደረጃ አምስት በሆቴልና በቱሪዝም ማኔጅመንት 128 ሰልጣኞችን አስመረቀ።

የዕለቱ የክብር እንግዳ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ክብርት ወ/ሮ ቡዜና አልከድር ለተመራቂዎች ባስተላለፉት መልዕክት የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ የሰለጠነ የሰው ሀይል በእጅጉ ወሳኝ በመሆኑ ተመራቂዎች በስልጠና ያገኙትን የሙያ ክህሎትና ፣ሙያዊ ስነምግባርን በመጠበቅ እንግዶችን ማገልገል ያለንን ቱሪዝም ሃብት ማስተዋወቅ ይጠበቅባቹኋል ብለዋል።

የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት በበኩላቸው የዘንድሮ ምረቃ በአንድ በኩል የኮቪድ መከሰት ስጋት ቢኖርም በሌላ መልኩ የኮቪድ ፕሮቶኮል በማማሏት ኢትዮጵያ የጉብኝት ደህንነት ማረጋገጫ ከዓለም የጉዞና ቱሪዝም ማግኘቷ፣ የዓለም ኮንፈረንስና ኮንቬንሽን ማህበር እና የዓለም አቀፍ የኢግዚቢሽን ኢንዱስትሪ ማህበር አባል መሆኗ እና የተጀመሩ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ለዘርፉ እድገት ትልቅ ተስፋ ነው ብለዋል።

ቱሪዝም በዋናነት ለሴቶች ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር የኢኮኖሚ ዘርፍ በመሆኑ የስልጠና ማዕከሉም በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሯ ጠቁመዋል።

አክለውም በንድፈ ሀሳብና በተግባር የቀሰሙትን እውቀት በሚኖራቸው የስራ ዓለም ተግባራዊ እንዲያደርጉ በማሳሰብ ለተመራቂዎች ያላቸውን መልካም ምኞት ገልጸዋል።

የማሰልጠኛ ማዕከሉ በባለፈው ዓመት በኮቪድ ወረርሽኝ ምክኒያት ተቋርጦ በነበረው የስልጠና መርሐግብር 425 ሰልጣኞችን በዚሁ ዓመት በየካቲት ወር ያስመረቀ ሲሆን ከነዚህ ተመራቂዎች 57በመቶ ሴቶች ናቸው ።

በምረቃው የተቋሙ የቦርድ አመራርና አባላት፣ባለድርሻ አካላት፣የተቋሙ መምህራንና ሰራተኞች፤ የተመራቂ ቤተሰቦችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።




**በኮምኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ**

**ሰኔ 2013 ዓ.ም**










# የአዲስ  ሰልጣኞች አቀባበል ተደረገ

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የመለመላቸውን ከ350 በላይ የአንደኛ ዓመት ሰልጣኞችን አቀባበል አደረገ፡፡

በመርሃ ግብሩ ላይ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ሁሉን አቀፍ ወደ ሆነው የቱሪዝም ዘርፍ እንኳን ደህና መጣችሁ ብለዋል፡፡ አዳዲስ ሰልጣኞች ወደ ዘርፉ እየተቀላቀሉ መምጣታቸው ለሀገራችን የቱሪዝም እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

የአካዳሚክና ምርምር ዲን አቶ አብርሃም ለገሰ በበኩላቸው የቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ የስራ እድል የሚገኝበት በመሆኑ ሰልጣኞች ጠንከረው በመማር ስኬታማ መሆን እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

የአስተዳደርና ልማት ዲኑ አቶ ዳንኤል በቀለ በበኩላቸው ተቋሙ በቂ የተግባር ስልጠና ቤተሙከራዎችና ግብዓቶች መኖሩን ገልጸው በቀጣይም የተሻለ አቅርቦትና ለመማር ማስተማር የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶች እንዲኖሩ እንሰራለን ብለዋል፡፡


በመድረኩ ላይ የተቋሙ የሰልጣኞች ስነምግባር ደምብ፣የኮቪድ 19 ፕሮቶኮልና የትምህርት አሰጣጥ ሂደቶች ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ገለጻ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም የማዕከሉ የቀድሞ ሰልጣኞች የነበራቸውን ልምድ ለአዲስ ሰልጣኞች አካፍሏል፡፡





# የማሰልጠኛ ማዕከሉ አገልግሎት ተወዳዳሪነት እንዲያድግ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ







የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል አሁን ካለው የቱሪዝም እድገት ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆን በአደረጃጀት፣በአሰራርና በሰው ሀይል የነበሩበትን ችግሮች በጥናት ለይቶ ከሰራተኞችና መምህራን ጋር ውይይት አድርጓል።

በውይይቱ ላይ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት በጥናቱ በተለየው መሰረት ተቋሙ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ የሚገኘውን የቱሪዝም ዘርፍ በሚመጥን መልኩ አዳዲስ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት፣ መዋቅሩን በማሻሻልና የሰው ሀይልን በማብቃት ተወዳዳሪ እንዲሆን ይሰራል ብለዋል::
የአስተዳደር ዲን አቶ ዳንኤል በቀለ በበኩላቸው ጥናቱ የተቋሙን የውስጥ ችግሮችን ያሳየ በመሆኑ የተለዩ ችግሮችን በቅደም ተከተል ለማስተካከል ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል። በተለይም የማዕከሉ የደምብ ማሻሸያ እስኪጸድቅ ድረስ የውስጥ መዋቅርን በማስተካከል የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል ብለዋል።
የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞችም እየተሰራ ባለው ጥናት ላይ ያላቸውን ማስተካከያ በማከል ማዕከሉ በተሻለ መልኩ የተሰጡትን የስልጠና፣ የጥናትና ምርምር እና ማማከር ተልዕኮ እንዲወጣ ለማድረግ ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸዋል።

## ለተቋም ለውጥ በቅድሚያ የሰዎች መለወጥ እንደሚያስፈልግ ተገለፀ





የማሰልጠኛ ማዕከሉ ተልዕኮውን እንዲወጣ የመዋቅርና አሰራር ማሻሸያ ጥናት ላይ ውይይት አካሄደ ።
የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል የስልጠና፣የጥናትና ምርምር እና የማማከር ተልዕኮውን ለመወጣት የሚያስችል የመዋቅርና አሰራር ማሻሸያ ጥናት አስጠንቶ ከሰራተኛው ጋር ውይይት አድርጓል።
ውይይቱን በንግግር የከፈቱት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ማዕከሉ የተሰጠውን ሀገራዊ ተልዕኮ በሚገባ ለመወጣት እንዲችል የቀረበው ጥናት ላይ የሀሳብ ግብዓት እንዲሰጥና በትኩረት እንዲከታተሉ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል።
የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል መምህራን የለውጡ መሪ እንዲሆን የሚያስችል ስልጠና ተሰጣቸው።
በኢትዮጵያ ማኔጅመንት ኢንስቲትዩቱ የስልጠና አማካሪ የሆኑት አቶ አብዱል ሃሊቅ ረሽድ እንደገለፁት ለአንድ ተቋም ውስጣዊና ውጫዊ ለውጥ በቅድሚያ መለወጥ ያለበት የሰዎች አሰተሳሰብ መሆን እንዳለበት ነው ።
ስለሆነም ለውጥ ተግባራዊ እንዲሆን የሰዎችን አሰተሳሰብ ሊገሩ የሚችሉ ሥራዎች ካልተሰሩ ወደ ግብ ለማድረስ ተቋማት እንደሚቸገሩ አሰልጣኙ ተናግረዋል።
በዚህ ስልጠና የተሳተፉ አሰልጣኞች ተቋሙ በራሱ ባለሙያዎች የተጠናውን መሠረታዊ የለውጥ ሰነድ ግብዓት ማሰባሰቢያ መድረክ ነው።








## ቱሪዝም ለሰላም ፤ሰላም ለቱሪዝም! በሚል ቃል የ8ኛው እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ተከበረ

የኢትዮጵያዊያን የእንግዳ ተቀባይነት ባህል ለቱሪዝም ልማትና ሀገራዊ አንድነት ጉልህ ሚና   እንዳለው ተገለጸ፡፡
አስደናቂ የእንግዳ ተቀባይነት ባህል ለቱሪዝም ልማትና ሀገራዊ አንድነት ጉልህ ሚና እንዳለው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ዶክተር ሂሩት ካሳው ተናገሩ፡፡
8ኛው የቱሪዝምና የእንግዳ ተቀባይነት ሳምንት "ቱሪዝም ለሰላም፤ ሰላም ለቱሪዝም" በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ ተካህደዋል፡፡
በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትሯ ዶክተር ሂሩት "የኢትዮጵያን የእንግዳ ተቀባይነት ባህል ከሌሎች አለማት ባህሎች ጋር በማቀናጀት ቱሪዝም ለሀገር የኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ መስራት ያስፈልጋል" ብለዋል፡፡
"እንግዳ ተቀባይነት የኢትዮጵያዊያን የተፈጥሮ መዋቅራዊ ስሪት ነው" ያሉት ሚኒስትሯ፤ "አስደናቂ የሆነው የእንግዳ ተቀባይነት ባህላችን ለቱሪዝም ልማት ብሎም ለሀገራዊ አንድነት ጉልህ ሚና አለው" ብለዋል፡፡
የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ አስቴር ዳዊት በበኩላቸው ማዕከሉ ከተመሰረተ ጀምሮ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉ ሙያዊ ብቃት ባላቸው አካላት እንዲመራ ለማድረግ በርካታ ሙያተኞች ማሰልጠኑን አስታውሰዋል፡፡
ፕሮግራሙም ለሶስት ቀናት የቆየ ሲሆን የተለያዩ በውስጡም ባህላዊና ዘመናዊ የምግብ ውድድሮች፣ በአማርኛ በእንግልዝኛና በፈረንሳይኛ የማስጎብኛት ውድድሮች እንዲሁም ጆፈር   ተካህዱዋል፡፡
የተቋማችን የቱሪምና የዕንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ሁለተኛ ቀን ፕሮግራም ተመርቀው የወጡ ሠልጣኞቻችንን የሥራ እድል ለማመቻቸት የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህም በጆፈሩ 23 ሆቴሎች፣1ሎጅ እና 2 ቱሪዝም ድርጅቶች በአጠቃላይ 26 ድርጅቶች ተገኝቶ 136 ሰልጣኞች ተመዝግበዋል፡፡











## የቱሪዝምን በዕውቀት በመምራት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ መስራት ይገባል ተባለ

የቱሪዝም ዘርፉን በዕውቀት በመምራት ገቢውን ለማሳደግ በሆቴልና ቱሪዝም ስራ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት እንደሚገባ የተቀቋማችን የቦርድ ሰብሳቢ የሳይንስንና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ አሳሰቡ።

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል ያዘጋጀው 8ኛው የቱሪዝም ሲምፖዚየም "ቱሪዝም ለሠላም፣ ሠላም ለቱሪዝም" በሚል መሪ ቃል ሲፖዚየም ተካሂዷል።

የቦርድ ሰብሳቢው ፕሮፌሰር አፈወርቅ ማዕከሉ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የቱሪዝም ስራ በመስራት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ መስራት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

ለዚህ ስኬት ይረዳ ዘንድ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ተቋሙ የበለጠ መስራት አለበት ብለዋል።

ማዕከሉ ለቱሪዝም እድገት አስተዋጽኦ ያላቸው ሁኔታዎችን በማጥናት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ እንደሚጠበቅበትም አሳስበዋል።

ኢትዮጵያ አገር በቀል ዕውቀቶችን ለመተግበር ይረዳት ዘንድ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን በማጣመር ተግባር ላይ ለማዋል እየሰራች እንደምትገኝ ጠቁመዋል።

በመሆኑም የቱሪዝም መስህቦቿን የበለጠ ለማስተዋወቅ በትምህርት የተደገፈ አካሄድ መከተል ይገባል ነው ያሉት።

የቱሪዝም ሃብቶቿን በቴክኖሎጂ በማስተዋወቅ ለጎብኚዎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስፈልግም ሚኒስትር ዴኤታው አመልክተዋል።

ቱሪዝምን የኢኮኖሚ ምሰሶ ለማድረግ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን የገለጹት ደግሞ የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ አስቴር ዳዊት ናቸው።


ማዕከሉ ባህልና እሴትን በመጠበቅና የቱሪስት መስህቦችን በማስፋት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ የሚያግዙ ባለሙያዎችን ለማፍራት እየሰራ ነው ብለዋል።




# የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባነት ሳምንት

















**የሽልማት ፕሮግራም ፎቶ በከፍል**